የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| 11ኛ ዓመት ቁጥር 13<br>11th year No 13 | | ሐረር ኅዳር ፱ ቀን 1999 ዓ.ም<br>HARAR Nov,18 2006 |
|---|---|---|
| *ያንዱ ዋጋ ብር 1.00*<br>Unit Price Br. 1.00 | *በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ* | *የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272*<br>P.O.Box |

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር 17/1999 ዓ.ም**

**የሐረር ሚሌኒየም በዓል አከባበር ምክር ቤት እና ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ---------------------------------------------------------ገጽ381**

## ደንብ ቁጥር 17/1999

## የሐረር ሚሊኒየም በዓል አከባበር ምክር ቤት እና ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የሐረር ሚሌኒየም በዓል የሐረር ከተማ ምሥረታ አንድ ሺኛ ዓመት፣ 12ኛው አለም አቀፍ ሐረሪዎች ቀንና የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል በአንድ ላይ በክልሉ እንዲከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሐረር ሚሌኒየም በዓል በከፍተኛ ድምቀት ለክልሉ ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አጋዥ በሆነ መልኩ ለማክበር የሚያስችል አቅም መፍጠር ተገቢ እንደሆነ በመታመኑ፣

ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት የሚያቀናጅ፣ የሚመራና የሚያስፈጽም የሚሌኒየም ም/ቤትና አካላትን በህግ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/97 አንቀጽ 32/2/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሐረር ሚሊኒየም ም/ቤት ማቋቋሚያ የመስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 17/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሚሊኒየም ማለት"፡- የሐረር ከተማ መቆርቆር አንድ ሺኛ /1000ኛ ዓመት ወይም የሐረር ከተማ የመጀመሪያው ሚሊኒየም ማለት ነው፣
2. "የሐረሪዎች ዓለም ዓቀፍ ቀን " ማለት ከኢትዮጵያውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች የመሠረቱት የሐረሪ ባህልና ታሪክ ማበልጸጊያ ቀን ነው፡፡
3. "12ኛው የሐረሪዎች ባህልና ስፖርት ፌስቲቫል" ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ በሐረሪዎች የሚከበረው የባህልና ስፖርት ፌስቲቫል ሲሆን፣ በሐረር ከተማ በክልሉ መንግሥት አስተናጋጅነት ሐምሌ ወር 1999 የሚከበር በዓል ነው፡፡
4. "የሐረር ከተማ ሚሊኒየም በዓል" ማለት በሐረር ከተማ በመድረክና በተለያዩ ፕሮጀክቶች ዓመቱን በሙሉ የሚከበር በዓል ነው፡፡
5. "የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል" ማለት፡- በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መሰረት ሦስተኛው ሺህ ከመግባቱ ቢያንስ ከሦስት ወር ጀምር ዓመቱን በሙሉ ያለውን ጊዜ የሚሸፈን ነው፡፡
6. "ብሄራዊ ሚሊኒየም ም/ቤት" ማለት፡- በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 117/97 መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር ብሄራዊ ም/ቤት ነው፡፡
7. "የሚሊኒየም ም/ቤት" ማለት በደንብ ቁጥር 117/1997ዓ.ም አንቀጽ 7(1) መሠረት የብሄራዊ ሚሊኒየም ም/ቤት አካል ሆኖ በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት በክልል ደረጃ የሚቋቋመው የሚሊኒየም ም/ቤት ነው፡፡
8. "ደንብ" ማለት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር ብሄራዊ ም/ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ 117/97 ነው፡፡
9. "ም/ቤት" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተቋቋመው የሐረር ሚሊኒየም በዓል አከባበር ም/ቤት ነው፡፡
10. "ክልል" ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ማለት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም ዓላማዎችና አደረጃጀት

### 3. ስለመቋቋም

1. የሐረር ሚሌኒየም በዓል አከባበር ም/ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

### 4. የም/ቤቱ ዓላማዎች

ም/ቤቱ ዓላማዎች::

1. መላው ኅብረተሰብ በልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ረገድ የጋራ የሆነ ሀገራዊ አመለካከት በመገንባት የተሻለ ገጽታ ያላቿ ኢትዮጵያን ለማየት ብሩህ ተስፋ ሰንቀ ወደ አዲሱ የኢትዮጵያ ሚኒሊየም እንዲሸጋገር የማስቻል፣
2. ኅብረተሰቡን በልማትና በመልካም አስተዳደር ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በማንቀሳቀስ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር የማስቻል፣
3. በመንግሥትና በህዝቦች ሙሉ ተሳትፎ የአገሪቱን መልካም ገጽታ ሊገነቡ የሚችሉ ብሔራዊ እሴቶቻችን ለመላው ዓለም በማስተዋወቅ አገሪቱን በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም፣ በንግድና በሌሎች መስኮች ተመራጭነት የሚያሰጣት መልካም ገጽታ እንዲገነባ የማስቻል፣
4. ለመላው ኅብረተሰብ፣ ለወጣቱ ትውልድ በአጠቃላይ ለመላው ዓለም ብሔራዊ ዓላማዎቻችንን ተልዕኮአችንንና የትኩረት አቅጣጫዎቻችንን የሚያመላክቱ ዐበይት መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የማስቻል::
በተጨማሪም የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል::
5. ለአንድ ሚሊኒየም ህያው የሆነው የሐረር ከተማ ታሪክ ዘላቂ ሊሆን የሚችለው በልማት ሲታጀብ ነው:: ለዚህም መንግሥት በቀየሳቸው የልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ አቅጣጫዎች ዙሪያ የጋራ አመለካከት ፈጥሮ መንቀሳቀስ፣
6. በቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት እንዲሁም ለአካባቢ እንክብካቤ ኅብረተሰቡ ሰፊ ዋጋ እንዲሰጥ ማነሳሳት፣
7. ሐረር ያለ ሐረሪዎች፣ ሐረሪዎች ያለሐረር ተጨባጭ ትርጉም ስለማይኖራቸው ብሄራዊ መኖሪያቸውን በተባበረ ጥረታቸው እንዲገነቡ ማነሳሳት:: ለዚህም በክልሉ ኢንቨስትመንት፣ ቱሪዝም፣ ንግድና በሌሉትም መስኮች ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚችሉ ማመልከት፣

### 5. የሚሊኒየም ም/ቤቱ አባላት

❖ ምክር ቤቱ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል::

1. ከክልሉ ም/ቤት አባላት
   የክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ፣ ም/አፈጉባኤ
   የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አፈ-ጉባዔና ም/አፈ-ጉባዔ
   የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች
2. የክልሉ ፕሬዚዳንትና ካቢኔ አባላት በሙሉ
3. መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት
   - ሐእልማ ተወካይ
   - የሳምቲ ልማት ማኅበር ተወካይ
   - የሐረሪ ክልል ሴቶች ማኅበር ሊ/መንበር
   - የሐረር ከተማ ን/ም/ቤት ሊ/መንበር
   - የሐረር ወጣት ማኅበር ተወካይ
   - የዕድርና አፎቻዎች ጥምረት ሁለት አባላት
   - የእስልምና ጉዳይ ም/ቤት ሊ/መንበር
   - የሐረር ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ
   - የሐረር የካቶሊክ ቤተክርስትያን ተወካይ
   - የሐረር ፕሮተስታንት ቤተክርስትያን ተወካይ
   - የሐረር ቀደመስቀል ቅ/ማኅበር ተወካይ
   - ዳሽን ባንክ ተወካይ
   - ወጋገን ባንክ ተወካይ
4. በፕሬዝዳንቱ የሚሰየሙ የግል ባለ ሀብቶችና ታዋቂ ግለሰቦች
5. ለበዓሉ አከባበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ ሌሎች አካላት፣
   - ከሐረሪ ክልል ውጭ የሚቋቋሙ ኮሚቴ ሊቀመናብርት
   - የንዑሳን ኮሚቴ ሊቀመናብርት
6. ከሌሎች መንግሥት አካላት
   - ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ
   - ኤች ኣይ ቪ (ኤድስ) ሴክሬታሪያት ኃላፊ
   - ዋና ኦዲተር ጽ/ቤት ኃላፊ
   - ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት
   - ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት
   - ቀበሌ መስተዳድር አስተዳዳሪዎች
   - ቋንቋ አካዳሚ ኃላፊ
   - ቅርስ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ
   - መብራት ኃይል ተወካይ
   - ቴሌኮሙኒክሽን ተወካይ
   - ፖስታ አገልግሎት ተወካይ
   - ሐረሪ ሬዲዮ ቴሌቭዥን ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ
   - ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ተወካይ
   - ስታትስቲክስ መ/ቤት ተወካይ
   - ሐረር ንግድ ባንክ ኃላፊ
   - የአገር መከላከያ ተወካይ
   - የሐረር ሚሊኒየም ጽ/ቤት ኃላፊ

### 6. የሚሊኒየም ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ም/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሀ ግብሮችን ፕሮጀክቶችን ለመንደፍ የሚያስችል ሀሳብ ያቀርባል፣
2. የብሔራዊ ሚሊኒየም ምክር ቤት አካልና የሐረር 1000ኛ ዓመት በዓል የ12ኛው የሐረሪዎች ባህልና ስፖርት ፌስቲቫል አዘጋጅ ም/ቤት በመሆን ያገለግላል::
3. ለበዓሉ አከባበር የሚደረገው ዝግጅት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ድርጅቶች በአጠቃላይ መላው ህብረተሰብ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል፣
4. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

## ክፍል ሦስት

## ስለምክር ቤቱ አካላት

### 7. የሚሊኒየም ም/ቤት አካላት

ምክር ቤቱ

1. የሚሊኒየም አብይ ኮሚቴና ንዑሳን ኮሚቴዎች
2. የሐረር ሚኒሊየም ጽ/ቤት ይኖረዋል

### 8. የአብይ ኮሚቴ አባላት

1. የአብይ ኮሚቴው አባላት 11 ይሆናሉ፣
2. የአብይ ኮሚቴ አባላት
   - የሐረሪ ህ/ክ/መ/ፕሬዚዳንት ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚወከል :- ሰብሳቢ
   - የሐረሪ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ፣ አባል
   - ህዝብ አደ/ባ/ማ/ጉ/ቢሮ አባል
   - ሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም አባል
   - ትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ አባል
   - ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ አባል
   - ን.ኢ. ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ አባል
   - ፍትህ ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አባል
   - ለበዓሉ አከባበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁለት አባላት
   - የሐረሪ ሚሊኒየም ጽ/ቤት ኃላፊ አባልና ፀሐፊ

## 9. የአብይ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የም/ቤቱ አብይ ኮሚቴ

1. የም/ቤቱን አስተያየት መሰረት በማድረግ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሀ-ግብሮችን ፕሮጀክቶችንና የአፈጻጸም እቅዶችን በመንደፍ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶችና ንዑሳን ኮሚቴዎች እንዲፈጽሙ ያደርጋል፣
2. ለዓማው መሳካት ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣
3. የሐረር ሚሊኒየም በዓል አከባበር ሲጠናቀቅ በሥሩ በመከናወን ላይ ያሉትን መርሀ-ግብሮችና ፕሮጀክቶችን ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ በማስወሰን አግባብ ላላቸው መንግሥት አካላት ያስረክባል፣
4. የሚሌኒየም ጽ/ቤቱን በበላይነት ይመራል፣
5. በሐረር ከተማና በተለያዩ ከተሞች የም/ቤቱን ዓላማ የሚያስፈጽሙ ኮሚቴዎችን ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን እንዳስፈላጊነቱ እንዲቋቋሙ ይደርጋል፣ አመራር ይሰጣል፣
6. የሐረር ሚሊኒየም ጽ/ቤት የየሴክተር መ/ቤት ኮሚቴዎች፣ የተለያዩ ከተማ ኮሚቴዎችና የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዕቅድ ያፀድቃል፣
7. የሐረር ሚሊኒየም ጽ/ቤት በጀት ለመንግስት አቅርቦ ያፀድቃል አፈጻጸሙንም ይገመግማል፣
8. የሚሊኒየም በዓሉን ሌጎና ፓስተር ያፀድቃል፣
9. በየወሩ አንድ ጊዜ በመሰባሰብ አጠቃላይ እንቅስቃሴና ዕቅዶችን አፈጻጸም ይገመግማል፣
10. ለሐረር ሚሊኒየም በዓል አከባበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 10. የአብይ ኮሚቴ ሊቀመንበር

የአብይ ኮሚቴ ሊቀመንበር የክልሉ ፕሬዚዳንት ወይም በፕሬዚዳንት የሚወከል ሲሆን፣ ሊቀመንበሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡፡

1. ለአብይ ኮሚቴ የተሠጡ ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ መፈጸማቸውን በበላይነት ይከታተላል፣
2. የም/ቤቱንና የአብይ ኮሚቴውን ስብሰባ ይመራል፣
3. የአብይ ኮሚቴውና የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል፣
4. ለበዓሉ አከባበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 11. የሐረር ሚሊኒየም ጽ/ቤት

1. ጽህፈት ቤቱ
   - ሀ/ የራሱ የህግ ሰውነት ይኖረዋል
   - ለ/ የም/ቤቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይፈጽማል፣
   - ሐ/ ዕቅድ በጀትና አወቃቀሩን በአብይ ኮሚቴው አማካይነት ለመንግሥት አቅርቦ ያጸድቃል፣
   - መ/ ዋና ጽ/ቤቱ ሐረር ከተማ ሆኖ በአብይ ኮሚቴ ውሳኔ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል፣
   - ለ/ ከተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት የሚውጣጡና ሌሎች ጊዜያዊ ሠራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ይኖሩታል፡፡

## 12. የጽህፈት ቤት ኃላፊ

1. በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በመስተዳድር ም/ቤት ይሰየማል፡፡
2. የጽ/ቤቱ ኃላፊ የጽ/ቤቱን ሥራ በበላይነት የመምራት ኃላፊነት አለበት
3. ተጠሪነቱም ለአብይ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## 13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ ደንብ ከመፅደቁ አስቀድሞ በክልሉ ከፍተኛ አመራር ውሳኔ መሠረት በተቋቋመው የሐረር ሚሊኒየም ጽ/ቤት የተሰሩ ሥራዎች በዚህ ደንብ መሠረት እንደተከናወኑ ተቆጥሮ ህጋዊነታቸውን ይዘው ይቀጥላሉ፡፡

## 14. በጀት

1. የጽ/ቤቱ የሥራ ማስኬጃ በጀት በመንግሥት ይመደባል፣
2. ለበዓሉ አከባበር ዝግጅት የሚያስፈልገው ወጭ
   - ሀ/ በመንግሥት በሚመደብ፣
   - ለ/ በክልሉና ከክልሉ ውጭ በሚደረገው ኤግዚቢሽኖች ባዛርና ሌሎች የገቢ መሰብሰቢያ መድረኮች በሚገኝ ገቢ
   - ሐ/ ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ተቋማት ድጋፍ እና፣
   - መ/ ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚገኘው ገንዘብ በክልላዊ ጽህፈት ቤቱ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ሆኖ ለበዓሉ ዝግጅት ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

## 15. ስለ ሂሳብ መዛግብት

1. ጽ/ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ይመረመራል፡፡

## 16. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

አብይ ኮሚቴው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 17. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ኅዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሐረር ኅዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት